# ከአፈርኩ አይመልሰኝ ለመንግሥት አይበጅም

የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ሊቀመንበር ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ከሌሎች የቀድሞ የቅንጅት አመራሮች ጋር ሐምሌ 13 ቀን 1999 ዓ.ም. ከእስር የወጡበትን ሂደትና አፈፃፀም የድርጊቱ ዋንኛ ተዋናይ የነበሩ ሽማግሌዎች ዛሬ አደባባይ ወጥተው ሊናገሩት ባይደፍሩም በወቅቱ የሰጡት የፅሑፍ መግለጫ በቂ ምስክር ነው፡፡

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በአውሮፓ የፓርቲ ተልዕኳቸው ወቅት የተናገሩትም ሽማግሌዎቹ ሐምሌ 13 ቀን 1999 ዓ.ም. ባወጡት መግለጫ ከገለፁት እውነት የተለየ አይደለም፡፡ በሀገሪቱ ፕሬዝዳንት ተፈርሞ በተሰጣቸው የይቅርታ ምስክር ወረቀት ላይ የሠፈረውን ቅደመ ግዴታ የሚጥስ ነው ተብሎ ከተገመተ ይህን ግምት ያሳደረው ማንም ይሁን ማን ጉዳዩ መታየት የነበረበት በአዋጅ ቁጥር 395/96 አንቀጽ 4(3) መሠረት በይቅርታ ቦርዱ ነበር፡፡

ነገር ግን የፌደራል ፖሊስ ይህን የሕግ ሥርዓት በመተላለፍና ከየት እንዳገኘው በማይታወቅ ሥልጣን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ጠርቶ «ይቅርታ አልጠየኩም ብለሻል፡፡ ይህን ካላስተባበልሽ ይቅርታው ተሠርዞ ወደ ነበርሽበት እሥር ቤት ትመለሻለሽ» ከማለት አልፎ ይህንኑ በመገናኛ ብዙሀን በመግለፅ በማን አለብኝነት የመጀመሪያውን የህግ መተላለፍ ድርጊት ፈፀመ፡፡

ይህ ፖሊስ የፈፀመው ተግባር አግባብ እንዳልሆነ ሲነገረው ቆም ብሎ የሠራውን ከህግ አንፃር መርምሮ ማስተካከል ሲገባው «ከአፈርኩ አይመልሰኝ» በማለት «የሦስት ቀን የጊዜ ገደብ ሰጥቼሻለሁ» ወደሚል ማስፈራሪያ ተሸጋገረ፡፡

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ «ቃሌ» በሚል ርዕስ ባሠራጬት ፅሑፍ «በሽማግሌዎች የእርቅ ማግባቢያ መንፈስ መሠረት በፖለቲካ የተቀሰቀሰውን ክስ ፖለቲካዊ እልባት ለመስጠት ሰኔ 11 ቀን 1999 ዓ.ም. በተፃፈው ሰነድ በሽማግሌዎች አማካኝነት መንግሥትና ሕዝብን ይቅርታ ጠይቄአለሁ፡፡ ይህ ብፈልግም ልለውጠው የማልችለው ሃቅ ነው፡፡» በማለት የነበረውን እውነት አሰረድተው አነጋገራቸው የተዛባ ነወ ቢባል እንኳን ሊጠይቃቸው የሚገባው ቦርዱ መሆኑን ገለፁ፡፡

በዚህ ወቅት ፖሊስ ከድርጊቱ ሊታቀብ የይቅርታ ቦርዱም ጉዳዩን በህግ አግባብ ሊመረምር በተገባ ነበር፡፡ ነገር ግን ለህጉ ምንም ቦታ ሳይሰጥ ትዕዛዛቸው ያለመፈፀሙ እና ማስፈራሪያቸው ያለመሥራቱ ውርደት መስሎ የተሰማቸው ወገኖች በጀመሩት ከአፈርኩ አይመልሰኝ ድርጊታቸው ቀጥለውበት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ወደ ወህኒ አወረዷቸው፡፡

ፌደራል ፖሊስ፣ ፍትህ ሚኒስቴር፣ የይቅርታ ቦርድ፣ የፕሬዝዳንቱ ቢሮ እያንዳንዳቸው በሕግ የተከለለ የሥራ ድርሻ አላቸው፡፡ የእነአፄ በጉልበቱና የማንአለብኝ ቤት ካልሆነ በስተቀር አንዱ ሌላውን ተክቶ፣ የሥልጣን ክልሉንና የሥራ ድርሻውን ሕግ ከሚፈቅደው አሳልፎ ጠሪ፣ አስፈራሪ፣ አሳሪ ሊሆን አይችልም፡፡

የወ/ት ብርቱካንን ይቅርታ መነሳትና ወደ ወህኒ መውረድ የገለፀው የፍትህ ሚኒስቴርም ፖሊስ የፈፀመውን ስህተት ማረም ያለበት የህግ አካል ሆኖ ሳለ የፖሊስን ጥፋት አጠናክሮ ራሱም ህግ ስልጣን ባልሰጠው ጉዳይ ውስጥ ሆኖ ተጨማሪ የህግ መተላለፍ ፈፀመ::

ፖሊስ ያለመጥሪያ በቃል ትዕዛዝ ብቻ ቢሮ አስጠርቶ ማሰጠንቀቂያ የሰጣቸውን ህጋዊ ሰው በሕጋዊ መንገድ በመጥሪያ የተፈለገው ቦታ ድረስ መጥራት እየተቻለ ይህንንም ለማድረግ ፈቃደኝነቱ ከጠፋ በያታ ተመሳሳይ የሆኑ ወታደሮችን በመላክ በህጋዊና ሠላማዊ መንገድ መያዝ ሲቻል 10 ወንድ ታጣቂ ያሰማሩበትና በታጣቂዎቹም የተፈፀመው ስድብ፣ ማመናጨቅና ማንገላታት ህግ መጣስ ብቻ ተደርጐ የሚወሰድ ሳይሆን፤ ሽብር መንዛትና ሌላውን ለማሸማቀቅ ተብሎ የተፈፀመ ድርጊት መሆኑን ስለ ህግ የበላይነት የሚቆረቆር ዜጋ ሁሉ የሚገነዘበው ነው:: ከዚህም በላይ መሣሪያ የታጠቀ የፖሊስ ኃይልን ለማስፈራሪያ መጠቀም፤ ሲቪል የለበሱና የታጠቁትን ሽጉጥ እያሳዩ በፓርቲ ጽ/ቤት በር የሚያንዣብቡና ወጪ ገቢውን የሚያስፈራሩ ሰዎችን ማሰማራት አሁን ያለነው በህግ የሚተዳደር ሥርዓት ውስጥ ነው ወይስ በፖሊስ አስተዳደር (Police State) ውስጥ ነው? የሚለውን ጥያቄ እንድንጠይቅ ያደርገናል::

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ቃሊቲ ወህኒ ቤት ከገቡም በኋላ እስከ ዛሬዋ ዕለት ድረስ ምንአልባትም እስከ መቼ ሊቀጥል እንደሚችል በማይታወቅ ሁኔታ ከሌሎች እስረኞች ጋር እንዳይገናኙ ተደርጐ ለብቻቸው ነው የታሠሩት:: በህገ-መንግሥቱና በዓለም አቀፍ ህግ የተከበረ መብታቸው ተጥሶ ከእናታቸውና ከህፃን ልጃቸው በስተቀር ሌላ ወዳጅ ዘመድ እንዳይጠይቃቸው ተከልክለዋል::

ይህ ሁሉ ህገወጥ ድርጊት ወ/ት ብርቱካንን በተናጠል ለማጥቃት ብቻ ተብሎ ሳይሆን አንድነት ፓርቲን ለማዳከም ሌሎች ተቃዋሚዎችንም በማስፈራራትና «ይህን ያየህ ተቀጣ» በሚል ታስቦ የሚፈፀም ነው:: ይህ ግን በዛሬዋ አለም የሚሠራ አይደለም::

ለለውጥ የተነሱ ግንባር ቀደም ታጋዮችን በማሠር በማንገላታት ከዚህ አልፎም በመግደል ዓላማቸውን ማጥፋት ራዕያቸውንም መገደል እንደማይቻል ከሃያ ዓመታት በኋላ ሰሞኑን እውን የሆነው የማርቲን ሉተር ኪንግ ህልም ሊያስተምረን ካልቻለ በእርግጥም ኋላቀርነታችን በኢኮኖሚ ልማት ብቻ ሳይሆን በአዕምሮአዊ ልማትም ጭምር ነው ማለት ነው:: ይህ ደግሞ ከዛሬው ይልቅ የነገውን ችግራችንን የከፋ ያደረገዋል::

የሰው ልጅ የለውጥ ፍላጐት በአፈና ሊቆም እንደማይችል ለሚረዱ መልሱ ወቅቱ የሚጠይቀውን ለውጥ ማምጣት ነው:: ለውጥ ደግሞ በእልካዊና ግትራዊ ድርጊት የሚመጣ ሳይሆን አንዱ የሠራውን ስህተት ሌላው በአግባቡ እያረመ፣ ትናንት የመጡበትን መንገድ ዛሬም የሚገኙበትን አቅጣጫ ቆም ብሎ ከፓርቲ በላይ ሀገርን፤ከራስ ጥቅም በፊት የሕዝብ ዕድገትን በሚያስቀድም አስተሳሰብ መገምገምን ይጠይቃል::

ከምንም ነገር በላይ ለሥልጣንና ለግልም ሆነ ለቡድን ጥቅም ቅድሚያ በመስጠት አጥፊዎች በጥፋታቸው ከቀጠሉና የህግ የበላይነት ከዕለት ወደ ዕለት የሕዝብን አመኔታ እያጣ፣ የበታቾች ጥፋት ከፖለቲካ አንፃር ብቻ በማየት የላይኞቹ እያበረታቱት ወይንም አይተው እንዳላዩ እያለፉት አጠቃላይ

ሁኔታው በዚህ መልኩ የሚሄድ ከሆነ የሀገሪቱን የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በእጅጉ የሚጐዳው ይሆናል፡፡

ስለሆነም በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ እየተፈፀመ ያለው ህገ-መንግሥትን የጣሰ ተግባር ሠላማዊ ትግሉን ብሎም አጠቃላይ ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የሚደረገውን ሀገራዊ እንቅስቃሴ የሚያደናቅፍ በመሆኑ ህገ-መንግሥታዊ መብታቸው ተከብሮ ወዳጅ ዘመድ እንዲሁም የሞያና የትግል ጓዶቻቸው እንዲጐበኞቸው እንዲደረግ፡፡ እንዲሁም ከመነሻው ጀምሮ የተፈፀመው ድፍረት ፈፅሞ የህግ መሠረት የሌለውና መንግሥትም ለሠላማዊ ትግሉ መጐልበት ፍላጐት የሌለው፣ ለመድብለ ፓርቲ ፖለቲካ ያልተዘጋጀ፣ ከሁሉም በላይ የአንድን ፓርቲ የበላይነት ለማረጋገጥ ሲባል የሚፈፅማቸው ተግባራት የህግ የበላይነትን የማያከብሩ መሆኑን ከማጋለጥ ባለፈ የሚያስገኝለት ጥቅም እንደማይኖር እየጠቆምን የሁላችንም በሆነችው ኢትዮጵያ ሀገራችን በጋራ በመኖር ከሁሉም በፊት የህግ የበላይነት መረጋገጥ ወሳኝ መሆኑንና ራዕይ ያላቸውን ፖለቲከኞች በማሠር ሠላማዊ ትግሉን ማደናቀፍ ሀገራዊ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑን ሥልጣን ላይ ያሉ ወገኖች ሊገነዘቡት ይገባል፡፡ ለዚህ ደግሞ ዛሬ ቃሊቲ ያሉትን የደርግ ባለሥልጣኖች ሁኔታ ማሰብ ጠቃሚ ሳይሆን አይቀርም፡፡